በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ልጆች፣ ቤተሰባዊ ሕይወትና ምጣኔ

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
ጥር ፳ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ የቱ ነው?

- ልጆቻቸው በመልካምና ደጋግ ሰዎች ተከብበው በበጎነት የሚፈርዱ ሆነው ያድጉ ዘንድ ስለልጆቹ ደኅንነት የሚጸልይ

- በማዕድ፣ ከቤት ሲወጡ፣ ከመኝታ አስቀድሞ ከልጆቹ ጋር የሚጸልይ፣

- ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረው ጤናማ ግኑኙነት ዘወትር ፈቃዱን የሚጠይቅ

- ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ታናሽ፤ ሕይወት ያላት ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች የሚያስተውል

- ልጆቹ በቤተክርስቲያን፣ ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል፣ በሰንበት ት/ቤም ያላቸውን ተሳትፎ ዘወትር የሚከታተል

- የተወደደና ጸጥታ የሰፈነበት ዓለምን ለቤቱ የሚፈጥር

- በቤቱ ቅዱሳን ሥዕላት፣ መስቀል፣ ቅዱሳት መጻሕፍትና መንፋሳዊ መዝሙራት ያሉት

- በእያንዳንዱ ዕለት የነገሮች ክንዋኔ እግዚአብሔርን የሚያመሰግን

- ብዙ ጊዜውን ከልጆቹ ጋር በመጫወት፣ በማንበብና አስተማሪ የሆኑ የሕፃናት ፊልሞችን በመመልከት ለማሳለፍ የተቻለውን ሁሉ ጥረት የሚያደርግ

# ለልጆች ሥነምግባር - ከኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን

ልጆች የሚከተሉትን ድርጊቶች እንዲከታተሉ ማስተማርና ማለማመድ

- የሌሎችን ንብረትና መብት እንዲጠብቁ
- በንግግር ወቅት እንዲሰሙ
- የቤቱን ሥርዓት እንዲያከብሩ
    - ከምግብ በፊትና በኋላ እጃቸውን እንዲታጠቡ
    - አሻንጉሊቶቻቸውንና መጫወቻዎቻቸውን ከተጠቀሙበት በኋላ በተገቢ ቦታ እንዲያስቀምጡ
    - የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባብ እንዲወጡ
- ትሑታን እንዲሆኑ፤ ለሰዎች ክብካቤ እንዲያደርጉና ሌሎችንም እንዲረዱ
- በርጋታ እንዲራመዱና እንዲናገሩ

# ልጆች ን መቅጣት - ከኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን

የሚከተሉት መንገዶች ልጆቻችንን በቀናነት ለማስተካከል ይረዱናል።

- ለበርካታ ልጆች ማስጠንቀቂያ ከበቂያቸው በላይ ነው
- ደጋግሞ የታዘዙትን ለመፈጸም ፈቃደኞች ካልሆኑ ወደ ልጆቹ ደረጃ በመውረድ ዓይን ለዓይን በመተያየት፣ በርጋታ በመያዝ ወይም በመንካት፣ ርኅራኄ በተሞላበት ያልተቆራረጠ ድምፅ እንዲያደርግ የፈለግነው ምን እንደሆነ መንገር ወይም ማስረዳት
- ለልጆች የሠሩት ስህተት ምን እንደሆነ ዘወትር እናስረዳቸው፣ ስህተት ምን እንደሆነ እንዲያስቡ ጥቂት ጊዜ የሠሩት ከሰጠናቸው በኂላ የሚጠበቅባቸው ምን እንደሆነ እንንገር
- የሚያናድድና የሚያስቆጣ ነገር ሲገጥመን እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት መዝሙር በመስማት፣ ሁኔታውን ከትዳር አጋራችን ጋር በመነጋገር ወይም በመጸለይ ጥቂት ጊዜ እንውሰድ። ይኸም ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን ከማድረግ እንድንቆጠብ የሚያደርገን ሲሆን መፍትሔም ለመፈለግ አማራኞችን እንድንመለከት ይረዳናል።
- ለልጆች አማራጮችን መስጠት ስህተቶቻቸውን እንዲያርሙ ይረዳቸዋል። (ምሳሌ፦ እራቱን በመብላት ፋንታ የሚጫወት ከሆነ #ትበላለህ ወይስ ትጫወታለህ; የሚል ምርጫ ስጧቸው። በምግቡ በመጫወቱ ከቀጠለ በሥርዓት የምግብ ጠረጴዛውን ለቆ እንዲሄድና ዝግጁ ሲሆን እንዲመለስ ያድርጉ)
- የሚሰሩትን ስህተታቸውን ተከትሎ የሚመጡ ነገሮችንም በኃላፊነት እንዲቀበሉ ማስተማር (ዕቃ ቢሰብር ተጨማሪ ሥራ በቤት ውስጥ እንዲሠራ ማድረግ)
- ከወላጆቻቸው ጋር ባልታረመ ንግግር ሲነጋገሩ በሌላ ክፍል በመቆየት በሥርዓት መናገር ስትችል እሰማሃለሁ በሉት።
- በእንግድነት ወደ ተጠራችሁበት ሥፍራ ከመሄዳችሁ በፊት ወዴት እንደምትሄዱና ምን እንደሚጠበቅባቸው አስረዷቸው።
- ልጁ ስህተት ከሰራና ስህተቱንም ለመረዳት የሚችልበት ዕድሜ ላይ ከደረሰ ስለ ኑዛዜ ማስተማር መልካም ነው።

# *የልጆች መታዘዝ - በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን*

ልጆች ለምን እንታዘዛለን ብለው ሲጠይቁ #እኔ ስላዘዝሁ ነው; በማለት ሳይሆን የሚከተሉትን በማለት እናስረዳቸው

- እግዚአብሔር ለእሱና ለሕጉ እንድንታዘዝ ስለሚጠይቀን
- እግዚአብሔር ከወላጆቻችን በጎውን ለመማር እንዲያስችለን እንድንታዘዛቸው ስለሚጠይቀን
- እግዚአብሔር ከሌሎች ጋር ባለን ግኑኙነት ሁሉ እንዴት መልካም ሰዎች መሆን እንዳለብን ስለሚያስተምረን
- ነጻነትም ሕግ ስለሚያስፈልገው

- ክርስቲያን መሆናችን የአራዊት ፓርኮችን ከመጎብኘት ልጆችም ጓደኞቻቸውን እንዳይጠይቋቸውና እንዳይጠየቁ እንዳይጫወቱም ስለማይከለክል ጥሩ ጊዜ እንዳይኖራቸው ከማድረግ ወላጆች መቆጠብ ይገባቸዋል።

# ልጆች ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ

- እንደ ዕድሜያቸው አንዳንድ ነገሮችን ራሳቸው እንዲያከናውኑ መርዳት
  - ልብሳቸውን መልበስ... የመጫወቻ ዕቃዎቻቸውን መሰብሰብ
- በገደብ ነጻነት እንዲኖራቸው ማድረግ
  - ወላጆች ከቲቪ ፕሮግራሞች መልካሞቹ ላይ በመወሰን ልጆች እንዲመርጡ ዕድል መስጠት
  - በልጆቻችን ባልንጀሮች ዘወትር ጥንቃቄ ማድረግ
    - ወደ ቤታችን እንዲመጡ በመጋበዝ ጠባያቸው ምን እንደሚመስል መመልከት
    - ስለነርሱና ስለወላጆቻቸው መጠየቅ፣ ከነርሱ የሚማሩት ምን እንደሆነ በመጠየቅ መስማት
  - ለልጆቻችን ባልንጀራ እንዴት እንደሚመርጡ እናስተምራቸው
    - በጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ ታሪኮችን ለልጆች ማንበብ
    - በወጣትነታችን ዕድሜ ስለነበረን ሄኔታ ማስረዳት
    - በጉዳዩ ዙሪያ ያለን አቋም ምን እንደሆነ መግለጽ
    - ባልንጀሮቻቸውን ባግባብ መምረጥ የሚያስችላቸውን ዕውቀት ከቤተክርስቲያንና ከቤተሰቦቻቸው እንዲያገኙ ማገዝ
    - በጉዳዩ ዙሪያ ያለን አቋም ምን እንደሆነ መግለጽ
  - ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው በአግባብ እየመሩ ማሳደግ
    ለምሳሌ ከባልንጀሮቻቸው ጋር ባላቸው ግኑኝነት ግጭት ፈጥረው መጥፎ ቃላትን ሲጠቀሙ ብናገኛቸው ለማስተማር የምንችልበት ጥሩ አጋጣሚ እንደተፈጠረ በመረዳት ቢያንስ የተጋጩትን በማቅረብ የሚከተለውን እናድርግ
    - የተከሰተውን ሁኔታ እንዲያስረዷችሁ ልጆቹን ጠይቋቸው
    - ጥፋተኛው ልጅ ምን እንደሚሰማው ጠይቁት
    - ሌላ ሰው ቢያሳዝነው ምን ሊሰማው እንደሚችል ጥፋተኛውን ልጅ ጠይቁት
    - የተጎዳው ወይም የተበደለው ልጅ የተሻለ ስሜት እንዲሰማው ምን ሊያደርግ እንደሚችል አጥፊውን ልጅ ጠይቁት

# የቀጠለ...

## የቤተክርስቲያን ተሳትፎአቸው

- ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሚከተሉትን መሆን ይችሉ ዘንድ ታላቁን ሚና ትጫወታለች
  - ስለ እግዚአብሔር የበለጠ እንዲያውቁ
  - ጠንካራ እምነት እንዲኖራቸው
  - ከኦርቶዶክሳውያን ጓደኞቻቸው ጋር ያላቸው ወዳጅነት የበለጠ እንዲጠነክር
  - ጠንከር ያለ ችግር ሲገጥማቸው ሊረዱ ወደሚችሉበት ሥፍራ መሄድ ይችሉ ዘንድ
  - የሚወዳቸውና የሚቀበላቸው ሕዝብ ያገኙ ዘንድ

## በጀታችንን እንዴት እናዘጋጃለን?

- እንደ ገቢያችን መጠን ምን ያህል ገንዘብ ለሚከተሉት እንደሚወጣ መወሰን፡-
  - ለእግዚአብሔር
  - ለልጆች ልብስ፤ ለልጆች የተለያዩ ፍላጎቶችና፤ ለመማሪያ (መለማመጃዎቻቸው)
  - ለምግብና ለመሳሰሉት የግሮሰሪ ወጪዎች
  - ለቤት ቁሳቁስ (ለጥገና፤ ለተለያዩ ወንበሮች...)
  - ለባልና ለሚስት ልብሶችና የተለያዩ ፍላጎቶች ማሟያ
  - ለመጓጓዣ
  - ለተለያዩ ወጪዎች (ለመብራት፤ ውሃ፤...)
  - ቁጠባ

# የቤተሰብ ምጣኔ

- እንደ አቅማችን፤ ማኅበራዊ ሁኔታዎች፤ የልጆቹን መንፈሳዊነት ቁሳዊና ማኅበራዊ ፍላጎት ለማሟላት እንደ መቻላችን መጠን ልጆችን ለመውለድ መወሰን ነው።

- የወላጁ ሚና ልጆችን በመውለድ ላይ የተገደበ ሳይሆን ይልቁኑ ልጆቹን በማሳደግ ላይም የሚያጠነጥን ነው።

- ወላጆች ልጆችን በማሳደግ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ከፍ ያለ ሊሆን ይገባል። ቤተክርስቲያንም ስለ ምጣኔ የምታስተምረው ትምህርት የሚመነጨው ከዚሁ ነው።

- በኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊ፤ መንፈሳዊ ምክንያቶች የተነሳ ወላጆች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያዳግታቸው ሁኔታ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። በዚህ የተነሳ የወሊድ መቆጣጠሪያ ጥያቄ ይነሳል። መነሻውም ወላጆች ለልጆቻቸው በቂ ክብካቤ ለማድረግ አለመቻላቸው ነው።

- ቤተክርስቲያን በወደፊቱ አገራዊ፤ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ በሚታዩ ችግሮችና ባሉ ስጋቶች ላይ በመመርኮዝ መንፈሳዊ አደራዋን ከመወጣት አንጻር የበኩልዋን አስተዋጽዖ ታደርጋለች።

- የጋራ የሆነ አስፈላጊነት ካላቸው ሁኔታዎች የተነሳ የቤተሰብ ምጣኔን አመለካከት እንቀበላለን። ነገር ግን ውሳኔው በየቤተሰቡ ሁኔታ የተመሰረተ ሆኖ የምንቀበለውም ተፈጥሮአዊ ዘዴውን ብቻ ነው።
- ስለዚህ የቤተሰብ ምጣኔ ውሳኔ እያንዳንዳችን ሁኔታችንንና ኃላፊነታችንን እስካወቅን ድረስ እንደያንዳንዱ ሰው ሁኔታ የሚወሰን ነው።

# የቤተሰብ ምጣኔ

1. የጋብቻ አንዱ ዓላማ ዘርን መተካት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጋብቻ ብቸኛው ዓላማ አይደለም፡፡ የክርስቲያኖች ጋብቻ ልጆች ባይወለዱም ጋብቻው በልጆች ባይባረክም እንኳን ተጠብቆ ይቀጥላል፡፡ በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት መካንነት ለፍቺ ምክንያት አይሆንም፡፡
2. ልጆች ከእግዚአብሔር የሚሰጡ በረከቶች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን ሲባርካቸው እንዲህ አለ #እግዚአብሔርም ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው፦ ብዙ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፡፡; ዘፍጥረት 9*1 አብርሃምንም #ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን ; ዘፍጥረት 12*2፤ #ዘርህንም እንደ ምድር አሸዋ አደርጋለሁ የምድርን አሸዋን ይቈጥር ዘንድ የሚችል ሰው ቢኖር ዘርህ ደግሞ ይቈጠራል፡፡ … ወደ ሜዳም አወጣውና፦ ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው፡፡ ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው፡፡; ዘፍጥረት 13*6፤ ዘፍጥረት 15*5 #ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና፡፡; ዘፍጥረት 17*5፤ #እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው፡፡; መዝሙር 127*3

- ሁሉም ዘር ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠ በረከት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም መመዘኛ አድርጎለታል፡፡ #ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ፡፡; ዘፍጥረት 17*21
- ቤተሰብ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው እውነተኛ በረከት መልካምና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልጆች ናቸው፡፡ የዔሊ ልጆች የተባረኩ አልነበሩም፡፡ ቀዳ. ሳሙ. 2*27-35፡፡
- ስለዚህ ዋናው ቁም ነገር የልጆቹ ጾታ ወይም ቁጥራቸው አይደለም፡፡ ወላጆች መደሰት የሚጠበቅባቸው በወለዷቸው ልጆች ብዛት ሳይሆን ለእግዚአብሔር፤ ለቤተክርስቲያንና ለኅብረተሰቡ በሚያቀርቧቸው ልጆች

# የቤተሰብ ምጣኔ

3. ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ከተፈጥሮ ጋር አይጋጭም፡፡
   - እግዚአብሔር ሴት ከተወሰነ ዕድሜ በኋላ እንዳትወልድ በማድረግ ተፈጥሮአዊ የሆነውን የወሊድ መቆጣጠሪያ ፈጥሮአል፡፡
   - ሴት መውለድ በምትችልበትም ዕድሜ በወር ውስጥ ዘር ማፍራት የምትችለው በተወሰኑ ቀናት ሂደት ብቻ ነው፡፡ በተቀሩት ቀናቶች ዘር ማፍራት አትችልም፡፡
   - ማንኛውም ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ በነዚህ ዘር ማፍራት በሚቻልባቸው ጊዜያት በጋብቻ ከሚኖር ግንኙነት በመታቀብ ሊፈጸም ይችላል፡፡
   - ይኽ ዘዴ በሴቲቱ ላይ መድኃኒት በመውሰድ ወይም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከሰተው ምንም ዓይነት ጉዳት የለም፡፡

4. በቤተክርስቲያን አጽዋማትና፤ ቅዱስ ቁርባን ከመቀበል በፊትና በኋላ ምዕመናን ከሥጋ ግኙኝነት ስለሚከለከሉ ይኽም ለቤተሰብ ምጣኔ እገዛ ያደርጋል፡፡

5. ጡት ማጥባትም እንደ ቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ያገለግላል፡፡

- ቤተክርስቲያን ሌሎችን የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች ምዕመናን እንዲጠቀሙ የማታበረታታው
  1. በእናቲቱ ሕይወት ላይ ከሚያስከትሉት አደጋ የተነሳ (እስከ ሞት አደጋ ያስከትላል)
  2. በአካላቶቻችን ላይ ከሚፈጥሩት መዘበራረቅ (ደም ማነስ፤ ወርሃዊ የሴቶች የተፈጥሮ ግዴታ ሂደትን ማዛባት፤ ለመውለድ ያለመቻል)
  3. ለግል ምቾት (ራስወዳድነት) ሲባል ልጅ ላለመውለድ በመወሰን የሚፈጽሙት ስላሉ

# ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ጠቀሜታዎች

1. ለሰውነታችን ጥንቃቄ ማድረግን በተመለከተ ከሰፋ ግንዛቤ ስለሚመነጭ ጤናማ በመሆኑ

2. ለእርግዝና መኖር፤ እርግዝናን ለማቆየት፤ ለማስወገድ በጣም ውጤታማ ዘዴ ስለሆነ።

3. ከአካባቢያዊ ጥበቃም አንጻር አዋጭና ጠቃሚ ስለሆነ
   - ለምሳሌ በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፡ የእርግዝና መከላከያ መድኃኒቶች ለበርካታ አደገኛ ከፈሳሽ ቆሻሻ የሚከሰቱ በሽታዎች ምንጭ ሆኖ ተጠቅሷል።

4. ባል ለሚስት አለመጎዳት አጋር ሆኖ ስለሚገኝበትና ለጋብቻው ሕይወት ጤናማነት ደጋፊ ስለሆነ።

5. ቀላል ባልም ሚስትም ለመማርም ሆነ ለመፈጸም የማይቸገሩበት ስለሆነ

6. ከወጪ አንጻር ውድ አይደለም።

7. ለመንፈሳዊ ሕይወትም ተደጋጋፊ ስለሆነ

# ጽንስ ማስወረድ የሚከለከልበት ምክንያት

ጽንስ እንደ ሰው የሚታሰበው ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር በማኅጸን ሳሉ ስለሠራው ሥራ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረዳን። ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ አትግደል የሚል ስለሆነና ማስወረድም እንደመግደል ስለሚቆጠር ነው።

1. ቅዱስ ዮሐንስ ሉቃስ 1:28

2. ሶምሶን ከመወለዱ በፊት እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን ነጻ ያወጣ ዘንድ ተመረጠ። መሳ. 13:2-5

3. ቅዱስ ጳውሎስ በማኅፀን ሳለ ለአሕዛብ ወንጌልን ይሰብክ ዘንድ ተመረጠ። ገላትያ 1:15

4. ኤርምያስ በማኅፀን ሳለ ለነቢይነት ተመረጠ። ኤርምያስ 1:5

5. የይሁዳው ንጉሥ ኢዮስያስ ከመወለዱ አስቀድሞ ስለመወለዱና ንጉሥ ስለመሆኑ ተነግሮለታል። 1ኛ ነገሥት 13:2 … ምሳሌ 23:26 ፤ ሕዝቅኤል 3:18-19

በርካታ የሕክምና ባለሞያዎችም ድርጊቱ ከክርስቲያናዊ እምነታቸው ስለሚጣላ አይፈጽሙትም። ይህም ያልተለመደ ከመሆኑ ይልቅ መለመዱ ይበልጣል - በርካታ ነርሶችና ዶክተሮች ከድርጊቱ ስለሚርቁ… ማስወረድ በጭካኔ የሰውን ገላ እየቆራረጡ የመጣል ድርጊት ነው።

***እግዚአብሔር አምላካችን በእመቤታችን አማላጅነት በሰው ነፍስ ከመጠየቅ ይጠብቀን።***

ወስብሐት

ለእግዚአብሔር፡፡